# ENGI FURNITURE

CREATIVE FOR TVC

# እንቁን በእንቁ መሀል

እንቁን በእንቁ መሃል ማስታወቂያ ቀላል እና ምናልባትም ፊትለፊት የሆነ አገላለጽን ተጠቅሞ የኤንጂ ፈርኒፈርን ታላቅ ዋጋ የሚገልጽ አካሄድ ነው፤  ታሪኩ ላይ የምናያት ሴት ወደ ጉዳይዋ ለመውጣት ስትዘጋጅ በመሃል ውድ የጆሮ ጌጥዋ ሲጠፋ እናያለን፤




መልኳ ባደረገችው ሰፊ
ኮፍያ እና መነጽር
የደበቀች እንስት ከመዋኛ
ገንዳ አጠገብ ጋደም ብላ
እናያታለን፤
ጸጥታ ሰፍኗል፤





ስልኳ ውስጥ ቴክስት ይገባል፤
*"ተዘጋጅተሻል ወይ"* ይላል፤






*ለስላሳ ጂንግል መጫወት ይጀምራል፤*

ከፑሉ ተነስታ በሳሎን በኩል ታልፋለች፤ በኤንጂ ፈርኒቸር የተዋበውን ሳሎን እናየዋለን፤





ልጅትዋ (መልኳን አላየነውም) በደስታ እና በአጫጭር ዳንስ መሰል ውዝዋዜዎች ታጅባ ልብሷን ጫማዋን ስታደርግ እናያታለን፤ በዚህ አጋጣሚ ውስጥም የመኝታ ቤቷዓን ፈርኒቸር እናደንቃለን፤





በድሬሲንግ ቴብል መስታወት ውስጥ ለመጀመሪያ ግዜ ሀናን እንደሆነች እናያለን፤ በመስታወቱ ስታይ አብረቅራቂ ጆሮ ጌጥ (ውድ የሚመስል) በአንደኛው ጆሮዋ ላይ ሲኖር በሌላኛው ጆሮ ላይ ግን እንደሌለ ትረዳለች፤ ዙርያዋን ትቃኛለች፤ አላገኘችውም፤





መኝታ ቤት ውስጥ መፈለጓን ትቀጥላለች፤ በመፈለግ ሂደቷ ውስጥ የአልጋውን ውበት እና ዩኒክነት እናደንቃለን፤ አልጋውን ከፍ አድርጋ ትፈልጋለች፤ ከስርም ትፈልጋለች፤ ምንም የለም፤



ሳሎን ቤት በተዋቡት ሶፋዎች መካከል መፈለግዋን ትቀጥላለች፤ የመፈለግ ሂደትዋ ሶፋዎቹን እድናደንቅ እና ሀሳባችን ወደዛ እንዲወሰድ ያደርጋል፤







በመፈለጓ ሂደት
ውስጥ  የፈርኒቸሮቹን
አስገራሚ ዲቴል
እንመለከታለን፤
ክራፍትስመንሺፑንም
እናደንቃለን፤

ሀናን በፍሊጋዋ ውስጥ
ብዙ አትረበሽም እስቲል
ደስተኛ ናት፤





ፍሊጋዋን
ቀጥላ ኮንሶል ቴብሉ ጋር
እና መሳቢያዎቹ ውስጥ
ትመለከታለች ፤ አልተገኘም



ሁለተኛ ግዜ ቴክስት
ይገባል፤
'ደርሰናል'ይላል፤




ሃናን ፍሊጋዋን ትታ
በመጀመሪያው ሙድ ፈታ
ብላ በውዝዋዜ ታጅባ
(ከጂንግሉ ቢት ጋር)
ትወጣለች፤



ሃነን ከወጣች በኋላ ያማረውን ፈርኒቸር እያየን፤

ትረካ(ወንድ)
የእርሶ የውድነት መገለጫ. . .




ካሜራው በዝግታ ከቲቪው መረድደሪያ ስር ወዳለ ትንሽ ካርድ ይጠጋል፤ I heart engi ከሚል የቢዝነስ ካርድ ጀርባ ጌጡ ተቀምጦ እናየዋለን፤

*ትረካ፡*

*. . . ይፈልጉት እንጂ ይገኛል፤*

*ኤንጂ ፈርኒቸር  የህይወቶ ልክ መገለጫ*

መጨረሻ